# ዘለቄታዊ የሳንቴሽን ጥምረት

## ወደ በለጠ ዘለቄታዊ የሳንቴሽን መፍትሄዎች

እትም 1.2 (እ.ኤ.አ. ነሐሴ 2009)

### *መግቢያ*

በሳንቴሽን ዘርፍ አፋጣኝ ሥራ መሰራት እንዳለበት ግልጽ ነዉ፡፡ ምክንያቱም በዓለም ላይ 2.6 ቢሊዮን ሕዝብ የተሻሻለ ንፅሕና የማያገኙ በመሆናቸውና 2.2 ሚሊዮን የሚሆኑ እድሜያቸው ከ5 ዓመት በታች የሆኑ ህፃናት በዓመት በሳንቴሽን ተዛምዶና በንፅህና ጉድለት ባላቸው በሽታዎች እየሞቱ መሆኑ ነው፡፡

የተባበሩት መንግስታት በኒዮርክ እ.ኤ.አ. በ2000 የሚሊኒየሙ ስብሰባ ላይ እና እንደ እ.ኤ.አ በ2002 በጆንሃንስበርግ የዓለም ዘላቂታዊ ልማት ስብሰባ ላይ ድህነትን ለማስወገድና ዘላቂ ልማትን ለማምጣት ተከታታተይ የምዕተ ዓመቱን ግቦች ቀርጽዋል፡፡ በመጠጥ ዉሃና ሳንቴሽን አገልግሎት በኩል የተቀመጠዉ አንዱ ዓላማ በዓለም ላይ ለንፁህ የመጠጥ ዉሃና መሠረታዊ የሳንቴሽን አቅርቦትን የሚያገኘዉን ህዝብ እ.ኤ.አ በ 2015 በግማሽ ለመቀነስ ነው፡፡

እ.ኤ.አ የ2006 የዓለም የጤና ድርጅት ዩኒሴፍ እና ዩኤን ዲፒ የሰው ኃይል እድገት ሪፖርት እንደሚያሳየው በሚሊኒየሙ የሳንቴሽን ግብ ለመምታት አዝጋሚ አካሄድ ያለው በመሆኑ በአሁኑ ጊዜ መሬት ላይ ካለው ሁኔታ ጋር ሲነፃፀር በጣም የተራራቀ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ በይበልጥ ጎልቶ የሚታየው ከሰሃራ በታች ባሉት አፍሪካ ሀገሮችና በከፊል እስያ ነው፡፡

ለዚህም በርካታ ምክንያቶች አሉ፡፡ ዋናው ጉዳይ ሳንቴሽን ለህብረተሰቡ በጣም ጠቃሚ ሆኖ ሳለ በፖለቲከኞች፣በሲቪል ማህበራትና በመሳሰሉት ተገቢዉን ትኩረትና ቅድሚያ አለማግኘት ነው፡፡ ሳንቴሽንን ቀዳሚ የዓለምአቀፍ የልማት አጀንዳ ለማድረግ የፖለቲካ ፈቃደኝነት በከፍተኛ ሁኔታ አይታይም፡፡ ለዚህም ምሳሌ የሚሆነው ሳንቴሽን በመጠጥ ዉሃ ፕሮጀክቶች መደበቁና በዘርፉም በጣም ጥቂት ፈጠራ መኖሩ ነው፡፡

በተባበሩት መንግስታት ውሳኔ አነሳሽነት እ.ኤ.አ 2008 የዓለም አቀፍ ሳንቴሽን ዓመት በመባሉ በሳንቴሽን ንቁ ተሳትፎ የሚያደርጉ ድርጅቶች የሳንቴሽን ዓመትን ለመደገፍ ግብረ ኃይል አቋቁመዋል፡፡
እ.ኤ.አ. በጥር 2007 በተደረገዉ የመጀመሪያ ስብሰባ ከተለያዩ ድርጅቶች የተገኙ አባላት በርካታ ስምምነቶችን አድርገዋል፡፡ እን ዲሁም በዚህ ስብሰባ በዓለም ዓቀፉ የሳንቴሽን ዓመት ዘለቄታዊ ሳን ቴሽንን ለማስተዋወቅና ለማስፋፋት የመጀመሪያ ረቂቅ የጋራ ፍኖተ ካርታ ሠነድ ተዘጋጅቷል፡፡ በሚያዚያ አጋማሽ ላይ በሁለተኛዉ ስበሰባ ወቅት የዓለም ዓቀፍ ብቃት መረብ ዓላማና ግብ ግልፅ ተደርጎ የጋራ ፍኖተ ካርታው ተከልሷል፡፡

ቡድኑ ለታቀዱት ሥራዎች የጋራ ስያሜ እንዲኖርና ተመሳሳይ ሃሳብ ካላቸዉ ጋር ለመጣመር "ዘላቂ የሳንቴሽን ጥምረትን (ሱሳና)" ቷል፡፡

### ዘለቄታዊ ሳንቴሽን ምን ማለት ነው ?

የሳንቴሽን ሥርዓት ዋና ዓላማ ንፁህ አካባቢን በመፍጠር እና የበሽታን ዑደት በመስበር የሰውን ልጅ ጤና መጠበቅ ነው፡፡ ዘለቄታዊ እንዲሆን ከተፈለገ ሳንቴሽን በጣም ውድ ያልሆነ፣ በህብረተሰቡ ተቀባይነት ያለው፤ በቴክኒካዊና በድርጅታዊ አወቃቀር ተስማሚ የሆነ ብቻ ሳይሆን አካባቢንና የተፈጥሮ ሃብትን የሚጠ ብቅ መሆን አለበት፡፡ አዲስ የሳንቴሽን ሥርዓት ሲዘረጋ ወይም የነበረው ሲሻሻል ከዘለቄታዊነት መመዘኛዎች ጋር ተዛማጅ የሆኑ የሚከተሉት ጉዳዮች መጤን አለባቸው፡፡



(1) **ጤናና ንጽህና፡-** በዚህ የሚጠቃለለው የሕብረተሰብ ጤናን የሚጎዱ በበሽታ አምጪ ተዋህስያንና አደገኛ ኬሚካሎች የመጋለጥ አደጋ ሲሆን ይህም በሁሉም የሳንቴሽን ሥርዓት ማለትም ሽንት ቤት ፍሳሽን መሰብሰብና ማጣራት እስከ ቆሻሻን በድጋሚ መጠቀምና ማስወገድ እና ወደ መጨረሻ ማስወገጃ አካባቢ የሚገኙ ሕዝቦችን ያጠቃልላል፡፡ ይህ ርዕስ በአንዳንድ የሳንቴሽን ሥርዓቶች የሚገኙ ከጤና፣ ከተመጣጠነ ምግብ፣ ከገቢ ምንጭ መሻሻል ጋር የተገናኙ ጉዳዮች እንዲሁም ከታች የሚመጡ ጉዳቶችን ያጠቃልላል፡፡









(2) **አካባቢና የተፈጥሮ ሀብት፦** ይህ ለሥርዓቱ ግንባታ፣ ኦፕሬሽንና ጥገና የሚያስፈልጉ የኃይል፣ የውሃ ሌሎች የተፈጥሮ ሃብቶች እንዲሁም በሥርዓቱ አጠቃቀም ወቅት ወደ አካባቢ የሚለቀቁ ነገሮችን ያካትታል:: ይህ በተጨማሪ እስከ ምን ያህል በተደጋጋሚና በድጋሚ የመጠቀም ልምዶችንና የእነሱን ውጠ ፥ቶችን (ለምሣሌ የቆሻሻ ውሃን ድጋሚ መጠቀምና ጠቃሚ ማዕድናትንና መበስበስ የሚችሉትን ለእርሻ መጠቀም) እና ሌሎች መታደስ የማይችሉትን ሃብቶችን መጠበቅ ለምሣሌ እንደ ባዮ ጋዝ ያሉ የሚታደስ የሃይል ማመንጫዎችን ማምረት::

(3) **ቴክኖሎጂ እና ኦፕሬሽን፦** ይህ የሚያካትተው በአካባቢው ህብረተሰብ ወይም በአገልግሎት ሰጪ ቴክኒክ ቡድኖች የሚሠራና በቀላሉ ሊገነባ፣ ኦፕሬት ሊደረግ፣ ለመከታተል የሚያመች፣ የአሰባሰብ፣ የማጓጓዝ፣ የማጣራት፣ መልሶ መጠቀም እና ወይም ማስወገድ የሚያስችል አጠቃላይ ሥርዓትን ነው:: በተጨማሪ ሥርዓቱ ጠንካራና ለመብራት መቋረጥ፣ ለውሃ እጥረት፣ ጎርፍ እና ለመሳሰሉት ካለው መሠረተ ልማት ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማቶች ጋር ሊስማማ እንደሚችል መገምገም ያለባቸው አስፈላጊ መስፈርቶች ናቸው::

(4) **የፋይናንስ እና ኢኮኖሚ ጉዳዮች፦** ይህ ጉዳይ የቤተሰብና የሕብረተሰቡ ለሳንቴሽን የመክፈል አቅም ጋር የተዛመደ ሲሆን ይህም በግንባታ፣ በኦፕሬሽን፣ በጥገናና ለሥርዓቱ የሚያስፈልጉ የወደፊት ኢንቨስትመንቶችን ያካትታል:: ከነዚህ ቀጥተኛ ወጪዎች ግምገማ በተጨማሪ ለምሣሌ እንደ አፈር ማበልፀጊያ ፣ ማዳበሪያ፣ ኃይልና የተጣራ ፍሳሽ ካሉ መልሶ ጥቅም ላይ የሚውሉ ነገሮች የሚገኙ ቀጥተኛ ጥቅሞች እና ተጨማሪ ወጪዎችና ጥቅሞች ከግምት ውስጥ መግባት አለባቸው፡ እነዚህ ተጨማሪ ወጪዎች እንደ አካባቢ ብክለና የጤና ጉዳቶች ሲሆኑ፤ ጥቅሞች ደግሞ- የእርሻ ምርታማነትንና ከእጅ ወደ አፍ የሆነውን ኑሮ ማሻሻል፣ ሥራ ፈጠራ፣ የተሻሻለ ጤና እና የአካባቢ አደጋን መቀነስ ያካትታል::

(5) **ሀገራዊ፣ ባህላዊ እንዲሁም ተቋማዊ ሁኔታዎች፦** በዚህ ክፍል መሥፈርቱ የሥርዓቱን ማህበራዊ፣ ባህላዊ ተቀባይነትና አግባብነት፣ አመቺነት፣ የሥርዓቱን ግንዛቤ፤ የጾታ ሚዛናዊነትና በሰብአዊ ክብር ላይ ያለውን ተፅእኖ፣ ለምግብ ዋስትና ያለውን አስተዋጽኦ፣ ካሉት ህጎችና ደንቦች ጋር አብሮ መሄዱን እና የተረጋጋና ውጤታማ ተቋማዊ አሠራሮችን ይገመግማል::

አብዛኛዎቹ የሳንቴሽን ሥርዓቶች የተቀረፁት ከፍ ብሎ የተጠቀሱትን ነጥቦች ባገናዘበ መልኩ ነው:: በተግባር ሲታይ ግን ሁሉም ሥርዓቶቹ ብዙውን ጊዜ ከላይ የተጠቀሱትን አንዳንድ መስፈርቶች ባለሟሟላታቸው ለውድቀት ተዳርገዋል:: በእውነቱ ከሆነ ፍጹም ዘለቄታዊ የሆነ የአሠራር ሥርዓት የለም:: የዘለቄታዊነት ጽንሰ ሃሳብ በአመዛኙ አቅጣጫ የሚያሳይ እንጂ ሊደረስበት የሚችል የሥራ ደረጃ አይደለም:: የሆነው ሆኖ ወሳኙ ጉዳይ የሳንቴሽን ሥርዓቶች ሲገመገሙ ሁሉንም የዘለቄታዊ አሠራር አቅጣጫዎች በጥንቃቄ ባካተተ መልኩ መሆናቸው ነው:: በተለያዩ ሁኔታዎች የዘለቄታዊ መስፈርቶችን የሚያሟላ አንድ ወጥ የሆነ የሳንቴሽን መፍትሄ ስለሌለ የሥርዓቱ ግምገማ በአከባቢው አደረጃጀት እና በአካባቢያዊ፣



ቴክኒካዊ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት:: የሳንቴሽን ሥርዓት ሲታቀድና ሲተገበር ሁሉንም የዘለቄታዊ መስፈርቶችን በመውሰድ አንዳንድ መሰረታዊ መርሆችን ማጤን አስፈላጊ ነው:: ይህም ከተወሰኑ ዓመታት በፊት በባለሙያዎች ተቀርጾና እ.ኤ.አ. በህዳር 2000 በተካሄደው አምስተኛ ዓለም ዓቀፍ ጉባኤ ላይ በመጠጥ ውሃና ሳንቴሽን መርሆች አስተባባሪ ምክር ቤት አባላት የቤላጂዮ የዘሌቄታዊ ሳንቴሽን መርሆች በመባል ፀድቋል፦

(1) ማንኛውም የሳንቴሽን ፅንሰ ሃሳብ የሰው ልጅን ክብር፣ የኑሮ ሁኔታ እና በቤተሰብ ደረጃ የአካባቢ ደህንነትን ማዕከል ያደረገ መሆን አለበት::

(2) የመልካም አስተዳደር መርሆዎችን በተከተለ መልኩ ውሳኔ ሰጪነት ሁሉንም የሚመለከታቸውን አካላት በተለይም የተጠቃሚዎችና አገልግሎት ሰጪዎችን ተሳትፎ ማካተት አለበት::

(3) ቆሻሻ እንደ ሀብት መቆጠር ያለበት ሲሆን አስተዳደሩ ደግሞ ሁሉን አቀፍና በተቀናጀ ውሃ ሀብት ልማት፣ የንጥረ ነገሮች ፍሰት እና የቆሻሻ አስተዳደር ሂደት አካል መሆን አለበት::

(4) የአካባቢ ሳንቴሽን ችግሮች የሚፈቱት በዝቅተኛ ተግባራዊ ሊደረጉ በሚችሉ እርከኖች (ቤተሰብ፣ መንደር፣ ቀበሌ፣ ከተማ ወረዳ፣ ዞን፣ ክልል) መሆን አለበት::

## የዘለቄታዊ ሳንቴሽን ጥምረት (ሱሳና) ግብና ዓላማዎች

የሱሳና አጠቃላይ ግብ ሁሉንም የዘለቄታዊ ጉዳዮች ከግምት ውስጥ ያስገቡ የሳንቴሽን ሥርዓቶች በማስፋፋት ለምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች አስተዋጽኦ ማድረግ ነው:: ሳንቴሽንን ከፍተኛ የፖለቲካ አጀንዳ ለማድረግ ስለሚረዱ የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች እና የተባበሩት መንግስታት ‘’አለማቀፍ የሳንቴሽን ዓመት እ.ኤ.አ. 2008’’ በከፍተኛ ሁኔታ በሱሳና አድናቆትን አግኝተዋል:: የዘለቄታዊ ሳንቴሽን ጥምረት ሥራ ዋናው ትኩረት የዓለም የጤና ድርጅት የተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም ፒኢፒ፣ ዩ.ኤን.ኤስ.ጅ ኤ.ቢ እና ዩኔስኮ በነደፉት ስትራቴጂዎች ጋር በተጣጣመ መልኩ ዘለቄታዊ ሳንቴሽን ሥርዓቶችን ትግበራ በትልልቅ የውሃና







የሳንቴሽን መርሃ ግብሮች ውስጥ ማስተዋወቅ ነው።



**ስለሆነም የሱሳና አጠቃላይ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፦**

- በዓለማችን ላይ ስለዘለቄታዊ ሳንቴሽን አሠራሮች ግንዛቤን መፍጠር እና በስፋት ማስተዋወቅ፤
- ዘለቄታዊ የሳንቴሽን ሥርዓቶች ለተከታታይ የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች (ለምሣሌ የህጻናትን ሞት ለመቀነስ፣ የፆታ እኩልነት ማስፈን እና የሴቶችን ተሳትፎ ማሳደግ፣ ዘለቄታዊ የአካባቢያዊ ደህንነትን ማረጋገጥ  የገቢ ምንጭን ማሻሻልና ድህነትን መቀነስ) ማሳካት እና ቅድመ ሁኔታ መሆናቸውን አጉልቶ መሳየት፤
- ሁሉም የሚመለከታቸውን አካላት በዘለቄታዊ ሳንቴሽን ፕሮጀክቶች እቅድ ጅማሮ ላይ እንዴት ተሳታፊ እንደሚሆኑ ማሳየት፣ የተጠቃሚዎችን ተነሳሽነትና ምርጫ ምላሽ መስጠት እና እነኚህም ለዘለቄታዊ የውሃና የፍሳሽ አስተዳደር  የሚሰጡ የንጽህና ትምህርትና አቅም ግንባታ ሥራዎች ጋር ጎን ለጎን መሄዳቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

**የሱሳና ንዑስ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው ፦**

- ውሳኔ ሰጪ አካላት በመረጃ የተደገፈ ውሳኔዎችን እንዲሰጡ ለማገዝ በሁሉም የዘለቄታዊ መስፈርቶች የታገዙ የተለያዩ የሳንቴሽን ሥርዓቶችና ቴክኖሎጂዎችን በመገምገም መረጃዎችን መሰብሰብና ማደራጀት፤
- አፈር ማበልጸጊያ፣ ማዳበሪያ፣ ባዮጋዝ፣ የኃይልና የመስኖ ውሃ የሚያስገኙ የሳንቴሽን ሥራዎች ከሳንቴሽን ባለፈ ለምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች መሳካት እንዴት አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ ማሳየት ስለዚህም ሙሉ ለሙሉ የቆሻሻ ማስወገድን  አመለካከት ለውጦ መልሶ የመጠቀምን አመለካከት ማምጣት፤
- ለዓለም ዓቀፍ የሳንቴሽን ዓመት 2008 እና ቀጣይ ጊዜያት በሳንቴሽን ዘርፍ ያሉ የተመረጡ የልምድ ተሞክሮዎችን ማሰባሰብና ማቅረብ ፤
- የድሃውን ሕብረተሰብ ተጠቃሚ ሊያደርጉ የሚችሉ አግባብነት ያላቸው የፋይናንስ አሠራሮችን ያካተቱ ብዙ ዘለቄታዊ የሳንቴሽን ዘዴዎችን በስፋት ለመተግበር የሚያስችሉ አሠራሮችን መለየት እና መዘርዘር፤
- ዘለቄታዊ አሠራሮች እንዴት የሳንቴሽን የምዕተ ዓመት የልማት ግቦችን ለማሳካት አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ እና እነዚህንም በዓለም ዓቀፉ የሳንቴሽን ዓመት እ.ኤ.አ. 2008 እና ቀጣይ ጊዜያት ማስተዋወቅ እንደሚያስችሉ ዓለማቀፋዊና አህጉራዊ ራዕይዎች መቅረፅ።

## ዓላማዎቹን እንዴት ማሳካት ይቻላል?

*የጋራ ፍኖተ ካርታ*

እነዚህን ዓላማዎች ለማሳካት እ.ኤ.አ. በጥር እና በሚያዚያ 2007 ከ 30 ከሚበልጡ ባለብዙ እና ሁለትዮሽ ስምምነት ያላቸው ድርጅቶች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና የምርምር ተቋማት የተወጣጡ ተሳታፊዎች ከዘለቄታዊ ሳንቴሽን ጋር የተገናኙ ሥራዎችን የተመለከተ ፍኖተ ካርታ ቀርጸዋል። ፍኖተ ካርታው በዋናነት  በዘለቄታዊ ሳንቴሽን ጉዳይ ላይ ሰፋ ያሉ ተከታታይ ህትመቶችን በጋራ የሚያወጡ፣ ዓለምአቀፋዊ ስብሰባዎችን የሚያስተባብሩ ወይንም ለስብሰባዎቹ አስተዋጾኦ የሚያደርጉ እና አዲስ የገንዘብ እገዛ ሥርዓቶችን እንዲሁም በዘለቄታዊ ሳንቴሽን የአቅም ግንባታ እና የፕሮግራም ጥንስሶችን ለመቅረጽ አስተዋጾኦ የሚያደርጉ የተለያዩ የሥራ ግብረሃይሎችን ያካትታል።

## “ ዘለቄታዊ የሳንቴሽን ጥምረት” ሌሎች እንዲሳተፉ ይጋብዛል

ሱሳና አዲስ ድርጅት ሳይሆን በተመሣሣይ የሥራ ዘርፍ ላይ በተሰማሩ ድርጅቶች የተቋቋመ ሆኖ ዘለቄታዊ የሳንቴሽን ሥርዓቶችን ለማስፋፋት በንቃት የሚሠሩ እና ሌሎች ከጥምረቱ ጋር አብረው ለመሥራት ለሚፈልጉ አካላት ክፍት የሆነ ላላ ያለ መረብ ነው። ዘለቄታዊ የሳንቴሽን ጥምረቱ ሌሎች ዓለም ዓቀፋዊ፣ ሀገራዊና ሀገር በቀል ድርጅቶች በመረቡ እንዲሳተፉ፣ ሃሳብ እንዲሰጡ እና በተለዩት የሥራ ቡድኖቾ ውስጥ በንቃት የሚሳተፉ አባላት እንዲሆኑ ይጋብዛል። ፍኖተ ካርታውን ለማሳደግ የሚሰጥ ግብረ መልስ በእርግጠኛነት ይበረታታል ምክንያቱም ሥራው በተከታታይነት የሚሻሻል እና ወደ ዘለቄታዊ ሳንቴሽን ሥርዓቶች ትግበራ የሚያመሩ ሁሉንም የጋራ እንቅስቃሴዎች ስለሚያካትት ነው።

**ለበለጠ መረጃ  የሚከተለውን  አድራሻ ይጠቀሙ፡**

info@susana.org
www.susana.org
Roland Schertenleib  (EAWAG – SANDEC)
Arne Panesar  (GTZ)







## ማጣቀሻ

**GTZ (2003):** “10 Recommendations for Action from the Luebeck Symposium on ecological sanitation, April 2003.”
http://www.gtz.de/de/dokumente/en-ecosan-recommendations-for-action-2003.pdf

**IWA (2007):** Sanitation21 – simple approaches to complex sanitation. A draft framework for analysis,
http://www.iwahq.org/uploads/iwa%20hq/website%20files/task%20forces/sanitation%2021/Sanitation21v2.pdf

**SEI (2005):** “Sustainable pathways to attain the Millennium Development Goals - Assessing the role of water, energy and sanitation”
http://www.ecosanres.org/pdf_files/MDGRep/MDG_folder.pdf

**SuSanA website:** **www.susana.org** – contains publications of working groups, case studies, minutes from SuSanA meetings, etc.

**UNDP HDR (2006):** Human Development Report 2006 - Beyond scarcity: Power, poverty and the global water crisis.
http://hdr.undp.org/hdr2006/pdfs/report/HDR06-complete.pdf

**UNDP PEP (2006):** “Poverty Environment Partnership Joint Agency Paper on Poverty Reduction and Water Management”
http://www.who.int/entity/water_sanitation_health/resources/povertyreduc2.pdf

**UNESCO-GTZ (2006):** “Capacity building for ecological sanitation.”
http://www2.gtz.de/Dokumente/oe44/ecosan/en-ecosan-capacity-building-2006.pdf

**UNSGAB (2006):** The Hashimoto Action plan http://www.unsgab.org/Compendium_of_Actions_en.pdf

**WHO (2006)**: Guidelines series on the safe use of wastewater, excreta and greywater in agriculture and aquaculture.
http://www.who.int/water_sanitation_health/wastewater/gsuww/en/index.html

**WSSCC/Sandec (2000):** The Bellagio Statement on Sustainable Sanitation:
http://www.eawag.ch/organisation/abteilungen/sandec/publikationen/publications_sesp/downloads_sesp/Report_WS_Bellagio.pdf

ሁሉም የSuSanA መሳሪያዎች በክፍት የመንጃ ፍቃዱ CC-BY SA ስር ይገኛሉ፡፡ ለጽሁፉ ትክክለኛ እውቅና መስጠት ሁል ጊዜ ቁሳቁሶች ጥቅም ላይ ሲውሉ መሰጠት አለባቸው፡፡
ይህ የፍቃድ መግለጫ SuSanAን ብቻ ያተኮረ ሲሆን፤ ነገር ግን ወደ SuSanA ቤተመፃህፍት ወይም SuSanA ድህረ ገፅ በተሰቀሉ ሌሎች ሰነዶች እና አቀራረቦች ላይ ብቻ የግድ አይደለም፡፡ በሌሎች ሰነዶች ላይ፤ እባክዎን የ SuSanA የፈቃድ ሁኔታዎች በጥንቃቄ ከመጠቀምዎ በፊት ያረጋግጡ፡፡ በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን ሁልጊዜ ትክክለኛ መግለጫ መስጠትዎን ያረጋግጡ፡፡

